# የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል የከዳ፣ የሕዝብን አደራ የበላና
# ለውጭ ጠላት የሚሰራ ዜጋ ዳግም ሕዝብን ማታለል አይችልም

በዘመነ ወያኔ በከፋ ሁኔታ የሚታየው አንዱ ገጽታ የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንዲሉ አገራችን አንዱ የሚሞትላት ሌላው የሚገድላት፣ አንዱ የሚዋጋላት ሌላው የሚወጋት፣ አንዱ የሚለፋላት ሌላው የሚከብርባት፣ አንዱ የሚንከራተትላት ሌላው የሚንቀባረርባት እየሆነች ለነጻነቷና ለሉዐላዊነቷ፣ ለሕዝቧ መብት መከበርና ለዲሞክራሲ፣ ለእድገትና ለብልጽግናዋ የሚታገልላት ሁሉ በውስጥና በውጭ ጠላቶቿ እየተጠቃ ትግሉ እየተጠለፈበት ይባስም ተብሎ ሙሉ በሙሉ ለወያኔና ለውጭ ጠላት ኃይል በመንበርከክ ሕዝብ ተስፋ ቆርጦ ለዘላለም በባርነት እንዲገዛ የሚናውዙ እየበዙ መሄዳቸው ነው::

ይህን መከራና ስቃይ በምርጫ 97 ለመገላገል ቆራጥ ልጆቿ ከጀግና መሪዎች ጋራ ተነስተው ወያኔን በሕዝብ ድምጽ በምርጫ ካርድ ከዘረሩት በኋላ፣ ከጥቂት ከሃዲዎች መካከል ደግሞ ትግሉን በመሸጥና በመክዳት ለወያኔ ቀጣይ እስትንፋስ ከሰጡትና የሕዝብ ትግል ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ከጨለሱበት ውስጥ አንደኛው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነው::

ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ወያኔ ሥልጣን ይዞ 41 የዩንቨርስቲ መምህራን ሲባረሩ በምትካቸው ሻንጣቸውን ቀርቅበው ከገቡት መካከል የሚጠቀስ ሲሆን የወያኔ አገዛዝ ተስማምቶት ሲያሻው አስተማሪ ሲያሻው ነጋዴ በመሆን ከወያኔ ሥርዓት ጋር ተስማምቶ የቆየ አድርባይ ምሁር ነው:: የምርጫ 97 ግርግር ለብዙዎቹ አመቺ ሁኔታን በመፍጠሩ በሶስት ወራት ውስጥ የትግሉ መሪና ዋና ተዋናይ በመሆን የራሱን የውስጥ ስራ ሲሰራ ቆይቷል:: ወያኔ የምርጫውን ውጤት ካጭበረበረና ሕዝቡም ተስፋው ተሟጥጦ ሰላማዊ ሕዝባዊ አመጽ ሊያነሳ ሲቆርጥ ነበር የዶክተር ብርሃኑ ሚና እየለየ የመጣው::

ዶክተር ብርሃኑ ነጋ በመስከረም ወር 1998 ዓ.ም በቅንጅትና ሕብረት የተጠራውን የቤት ውስጥ መቆየት አድማ ወይም የሙት አድማ ከሌላው ከሃዲ ከዶክተር በየነ ጴጥሮስ ጋር በመሆን አድማው ቀርቷል በማለት ከአሜሪካ ኤምባሲ በተሰጠው መመሪያ መሰረት በቴሌቪዥን ወጥተው በመናገሩ ወያኔን በአፍጢሙ ሊደፋው ተነሳስቶ የነበረውን ትግል አኮላሽቷል:: በዚህ የክህደት ተግባሩ ታሪክና የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅር የማይለው መሆኑን መዘንጋት የለብንም::

ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ቃሊቲ እስር ቤት በገባ በ6 ኛ ወሩ "የእኔ" "እኔ" ብቻ ታሪኩን "የነጻነት ጎህ ሲቀድ" በሚል ርዕስ ቆራጣ የኢትዮጵያ ካርታ ያለበትን መጽሐፍ "ወያኔ ሳያወቅ" "ከቃሊቲ እስር ቤት" ጽፎ ለንደን በአንዳርጋቸው ጽጌ ታርሞና "ጎረቤት አገር" ታትሞ 10 ሺህ ኮፒ አገር ቤት በኮንቴይነር ተጭኖ ገብቶ ተሸጦ እንደገናም ስንትና ስንት ሺህ ኮፒ አሜሪካ አገር ታትሞ በ35 ዶላር ተቸብችቦ ሕዝብን ጉድ አሰኝቶ ነበር:: ከ614 ገጾች ውስጥ አንድም ገጽ ስለቃሊቲ እስር ቤት ታሪክ አልተጠቀሰም:: ይህ ሁሉ እንዴት ሊሆን ቻለ? አንዳርጋቸው ጽጌ የመጽሐፉ ሽያጭ ለትግሉ ይውላል ብሎ ነበር የተከፋፈለው በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ገንዘብ የት ገባ? ዶክተር ብርሃኑ ከእስር ቤት ከወጣ በኋላ አንዲትም ቃል ስለመጽሐፉ አልተነፈሰም:: ለምን ? ጉድ እንዳይወጣ በመፍራት ነው::

ቃሊቲ እስር ቤት እያለ "ቅንጅት ኢንተርናሽናል ሊደርሽፕ" የሚለውን ቅንጅትን ለማፈራረስ የተቋቋመው ቡድን በእርሱ ትእዛዝ ነበር እነአንዳርጋቸው ጽጌና ብርሃነ መዋ ከውጭ፣ እነዶክተር ታደሰ ከአገር ቤት ተመሳጥረው ያን ተጋግሎ ዓለምን ያናወጠ ትግል ለማዳከምና ደጋፊውን ለመከፋፈል የቻሉት:: ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ከእነ አንዳርጋቸው ጽጌ ጋር በስልክ ይገናኝ እንደነበር፣ ቤቱም ማደር ይችል እንደነበር በቂ መረጃዎች ተገኝተዋል::

ዶክተር ብርሃኑ አንዳርጋቸው ጽጌን "እኔ የላዕላይ ምክር ቤት አባል አላደረኩትም" ብሎ ሲዋሽ አቶ አንዳርጋቸው ደግሞ "የቀስተደመና አባል ያደረገኝም፣ ቅንጅት የላዕላይ ምክር ቤት አባልም ያደረገኝ ዶክተር ብርሃኑ ነው" ይላል:: ሥራቸው ሁሉ የውሸት አካሄዳቸው ሁሉ የውሸት ነው:: ብርቱካን ሚዴቅሳንም በመስከረም መጀመሪያ የቀስተደመና አባል አድርጎ መስከረም 24 የቅንጅት ምክትል ፕሬዚዳንት እንድትሆን ያቀረባት ራሱ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነው::

አገር ቤት ለቅንጅት እርዳታ የተላከውን ገንዘብ ወደ ትውልድ አካባቢው ላለው ሕዝብ ይላክ ብሎ የወሰነው እና የላከው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነው:: ለመሆኑ የቅንጅት ዓላማስ ያ ነበር ወይ? ውሎ አድሮ ግን የዶክተር ብርሃኑ ሥራና ዓላማ በወያኔ የዘር ፓለቲካ ላይ ያመዘነ መሆኑ ተደርሶበታል:: በጣም የሚያሳፍር ወያኔያዊ ተግባር በቅንጅት ስም የፈጸመ ዘረኛ መሆኑን አስመስክሯል::

በብርሃኑ ነጋ ትእዛዝ አንዳርጋቸው ጽጌና ብርሃነ መዋ የውጭውን የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች በአውሮፓ ሙሉ በሙሉ በማፍረስ ጥቂት ቡድን ብቻ ሲቀር በአሜሪካና በካናዳ በየቦታው ሶስትና አራት ሰዎችን በማስከዳት ተለጣፊ ቡድን በመመስረት የመከፋፋልና የማዳከም ስራ ተሰርቷል:: ዋናው ተጠያቂው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነው::

እስር ቤት እያሉ ዘወትር "እኔ ውጭ ብወጣ ትግሉን እንዴት እንደምመራ አውቃለሁ" በማለት ያወራ የነበረውን ተግባራዊ ለማድረግ ሌላው እስረኛ ገና ከቤተሰቡና ከጎረቤቱ ጋር ናፍቆቱን ሳይወጣ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ቤተሰቡን ይዞ ሹልክ ብሎ ወጣ። በዱባይ አድርጎ፣ ለንደን ደርሶ አሜሪካ ተደብቆ ገብቶ ከነታማኝ በየነና ዶክተር ዓለማየሁ ገብረማርያም ጋር በመዶለት የአሜሪካውን ድራማ አዘጋጅተው ከጠበቁ በኋላ እነብርቱካን ሚዴቅሳ፣ ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራውና ዶክተር ኃይሉ አርዓያ ጋር ሲንሸራሸሩ ከርመው የውጭውን የቅንጅት ደጋፊ ከፋፍለውና አበጣብጠው በመቶ ሺዎች ዶላር ሰብስበው ሲመለሱ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ግን ወራጅ አለ አሜሪካ ሥራ ስላገኘሁ አልመጣም ብሎ ቀረ።

ለመሆኑ ሕዝብ መርጦ አደራ ከሰጠው እንዴት አድርጎ ነው የአንድ ዩንቨርሰቲ ውስጥ ሥራ ከአገሩና ከሕዝብ አደራ የበለጠበት?  ከቃሊቲ እስር ቤት ከወጣ በሳምንቱ አገር ጥሎ የወጣ እስካሁን የመመለሱን ነገር ጭራሽ አንስቶ አያውቅም። እንዲያውም ሥራ የሰጠው ዩንቨርስቲ እየከፈለው ቁጭ ብሎ እንዲያስብ አድርጎኛል ብሎ በስብሰባ ላይ በሕዝብ ፊት ተናገረ። ምን ማለቱ ነው? ማንን ነው የሚያሞኘው? ትግሉ ያለው አገር ቤት፣ የመረጠው ሕዝብ ያለው አገር ቤት ኒውዮርክ ተራራ ጫፍ ተቀምጦ ምንድነው የሚያስበው? እንደዚህስ ዓይነትስ መሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፈልጋል ወይ?  የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገውን ጠንቅቆ የሚያውቅ መፍትሔውም ትግሉም የት እንደሆነ በሚገባ የሚያውቅ ነው። ከአሜሪካ አገር ተራራ ላይ እንደመና የሚወርድለት ምንም ነገር እንደሌለ ያውቃልና ዶክተር ብርሃኑ ሌላ በውጭ ያለው ደጋፊ የሚታለልበትንና የሚከፋፈልበትን መንገድ አስቦ ለውጭ ጌቶቹ ለመንገር ከሆነ አያዋጣውም። ለአገሩ ያልሆነ ለሕዝቡ ያልሆነ ዜጋ ለሆዱና ለራሱ ብቻ ካልሆነ በቀር ቢጠቅም የኢትዮጵያን ጠላት ብቻ ነውና እዚያው ከተራራው ጫፍ ሳይወርድ ቢቆይ ለኢትዮጵያ ትልቅ ውለታ ነው።

ዶክተር ብርሃኑ ነጋ አገር ቤት ላለመመለስ ወስኖ ከቀረ ለምንድነው በቅንጅት ስም ሕዝብ እየሰበሰበ የሚነግደው? ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ጠቅላላ ጉባኤው እስኪወስን በቅንጅት ስም እንዳይንቀሳቀስ ከታገዱት አምስት ሰዎች አንደኛው ነው። ታዲያ ከብጤውና ከነጋዴው ደበበ እሸቱ ጋር በመሆን ሕዝብን ለምንድነው የሚያታልለው? የኢትዮጵያ ሕዝብ የእነብርሃኑ ነጋንም ሆነ ብርቱካን ሚዴቅሳን አንጃ ቡድን አልተቀበለውም። የቅንጅት አባላት እነዶክተር ብርሃኑ ነጋ፣ እነብርቱካን ሚዴቅሳ ማን እንደሆኑና ምን ዓላማ እንዳላቸው ዛሬ በሚገባ ስላወቃቸው በየክፍለሀገሩ ያሉት አባላቶች ዞር በሉልን እያላቸው ነው። የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች በተደጋጋሚ እያወገዟቸው ነው። በውጭም ያለው ክፍል እውነቱን አውቆ ከእውነተኛው ክፍል ጋር እየቆመ ነው።

ዛሬ እውነቱን አውቆ እየተንሰራራና ድጋፉን ለመስጠት ቆርጦ የተነሳውን ክፍል ለማወናበድና ለመከፋፈል የሚያደርገው እንቅስቃሴ መቆም አለበት። በአሜሪካ ከተሞችና በቅርቡ ደግሞ ወደ ካናዳም እንደሚመጣ ከአንዳርጋቸው ጽጌ ፓልቶክ ክፍል በመሰማት በቶሮንቶና አካባቢው የምንገኝ ኢትዮጵያውያን የዶክተር ብርሃኑን ነጋን ጸረ ቅንጅት እንቅስቃሴን በጥብቅ የምንቃወም መሆናችንና ይሄንን ሕዝብን የከዳ ግለሰብ የማንቀበለውና የምናጋልጠው መሆናችንን እናስታውቃለን።

የቶሮንቶና አካባቢው ነዋሪም ይህን የሕዝብን ትግል ከድቶ፣ ለውጭ ጠላት ተገዝቶ፣ የወያኔን አድሜ ለማራዘሚያ መሳሪያ የሆነውንና በውጭ ላለው ተቃዋሚ ኃይል መከፋፈል ቀጥተኛ ተጠያቂ በሆነው ግለሰብ ስብሰባ ላይ መገኘት ከኢትዮጵያ ጠላት ጋር መሰለፍ መሆኑን ተገንዝቦ በዚያ ዓይነት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይሳተፍ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የቶሮንቶና አካባቢው የትግሉ ተቆርቋሪዎችና ደጋፊዎች
ኤፕሪል 2008